# Seattle OED Business Stabilization Grant

## Introduction

**እባክዎን ያስተውሉ፡ ይህ ሰነድ ለ 6 ኛ ዙር የንግድ ማረጋጊያ ስጦታ ማመልከቻ መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን እንደተጠናቀቀ ማመልከቻ መቅረብ የለበትም። ምንም የወረቀት ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም**

## Introduction

የሲያትል የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (OED) በአነስተኛ ንግድ ማረጋጊያ ፈንድ (SBSF) ስድስተኛ ዙር በኩል አነስተኛ ንግዶችን ለማረጋጋት ተጨማሪ 4 ሚሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ እያደረገ ነው። በመላው ሲያትል በኮቪድ-19 በገንዘብ ለተጎዱ አነስተኛ ንግዶች የ 20,000 ዶላር፣ 10,000 ዶላር እና 5,000 ዶላር የእርዳታ ስጦታዎች አሉ። የአነስተኛ ንግድ ማረጋጊያ ፈንድ የዕርዳታ ስጦታዎች እንደገና የሚከፈሉ (ተመላሽ የሚሆኑ) አይደሉም። ይህ ፈንድ ቢያንስ በ 30% ድህነት ወይም ከ 60%
ይህ ማመልከቻ ከጥቅምት 19፣ ቀን 2021 እስከ ህዳር 9፣ ቀን 2021 ክፍት ነው። ስለ ምርጫ መመዘኛዎች እና የአሸላለም ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ድህረገፅ ይጎብኙ። ይህንን ማመልከቻ ለማጠናቀቅ ለእርዳታ፣ OED@seattle.govኢሜል ያድርጉ ወይም ወደ (206) 684-8090 ይደውሉ። የቋንቋ እርዳታ ይገኛል።

ማመልከቻዎን ከመጀመርዎ በፊት እባክዎ ልብ ይበሉ-

የጀመሩት መረጃዎን ማስቀመጥ (save) እና በኋላ ተመልሰው መጨረስ አይችሉም።
በአንድ ጊዜ መቀመጥ ውስጥ ማመልከቻውን ለማጠናቀቅ ይዘጋጁ (ከ20-30 ደቂቃዎች ይወስዳል)። ከመጀመርዎ በፊት እባክዎን የንግድ መረጃዎን እና የፋይናንስ ስራ ያዘጋጁ።
ሁሉንም ጥያቄዎች አስቀድመው ለማየት የማመልከቻ መመሪያውን መጠቀም ይችላሉ።
ዝቅተኛ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት መስፈርቶች

ለአነስተኛ ንግድ ማረጋጊያ ፈንድ (SBSF) ስጦታ ብቁ ለመሆን፣ ንግድዎ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡
አሁን የሚሠራ የሲያትል የንግድ ሥራ ፈቃድ ይኑርዎት።
የከተማ የንግድ እና ሥራ (B&O) ግብር ሙሉ በሙሉ እንዲከፈል ያድርጉ
ሁሉንም የፌዴራል፣ የክልል እና የከተማ ህጎች እና ደንቦችን ያከበሩ።
በሲያትል የከተማ ወሰኖች ውስጥ ይሁኑ (በዚህ ካርታ ያረጋግጡ )። በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ያልተቀላቀሉ (የማይገኙ) ንግዶች ለአነስተኛ ንግድ ማረጋጊያ ፈንድ (SBSF) ብቁ አይደሉም።
ሁለት ወይም ከዚያ ያነሱ ቦታዎች ያልዎት።
ከመጋቢት 1፣ ቀን 2020 ጀምሮ 50 ወይም ከዚያ ያነሱ የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች (FTEs) ያለዎት (ለማጣራት ይህንን የ FTE መቁጠሪያ ይጠቀሙ)።
በ 2019 እና 2020 በሲያትል ከተማ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በንግድ እና ሥራ (B&O) ግብሮች ውስጥ እንደተዘገበው ከ $ 1,000 ዶላር በላይ ያስገቡ እና በዓመት የተጣራ ከ $ 2,000,000 ዶላር ገቢ ያልበለጡ።
እስከ ጥቅምት 19፣ ቀን 2021 ቢያንስ ለ 24 ወራት በንግድ ሥራ ላይ ነበሩ።
በግል ባለቤትነት የተያዘ፣ ፍራንቻይዝ ያልሆነ (non-franchise) እና ያለ-ሰንሰለት (non-chain) የሆነ ንግድ።
በአፈፃፀም ጥበባት እና በአነስተኛ ንግድ ቴክኒካዊ ድጋፍ ላይ ያተኮረ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ይሁኑ
ከአካላዊ ሥፍራ ይሥሩ (ከፈጠራ ኢንዱስትሪዎች እና ከምግብ የጭነት መኪናዎች በስተቀር) በእኛ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች (FAQs) በሚለው ዉስጥ ስለ ኢንዱስትሪ ምድቦች የበለጠ ያንብቡ።
የአርሶ አደሮች ገበያ እና የተንቀሳቃሽ ሻጮች በአሁኑ ጊዜ በሲያትል ከተማ ውስጥ የንግድ ሥራ መሥራት እና በጣም የሚደጋገም የሲያትል አድራሻቸውን ማቅረብ አለባቸው።
የንግድ ሥራዎች ዓመታዊ የተጣራ ኪሳራ ለመዋጮ ስጦታው የተጠየቀውን ጠቅላላ የእርዳታ መጠን ወይም ከዚያ በላይ ሊሆን ይገባል (በሲያትል ከተማ የንግድ እና የሥራ መረጃ መሠረት)።
ንግዶች ብቁ የማይሆኑት የሚከተሉትን ካላደረጉ ነው፡

የንግዱ ባለቤት ወይም ሥልጣን የተሰጠው ተወካይ ለእርዳታ ስጦታው ያላመለከተ ከሆነ።
ንግዱ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የኪራይ ወይም የኢንቨስትመንት ንብረት ነው (የግል ሪል እስቴት (ገለልተኛ ሪልተሮች፣ የአጭር ጊዜ ኪራዮች አየርቢንቢ (Airbnb)፣ ቪርቦ (Vrbo)፣ ወዘተ) ያካትታሉ።
ንግዱ የታክሲ ስራ፣ በጋራ መሣፈር፣ ወይም የምግብ አቅራቦት አገልግሎት (እንደ ኡበር፣ ሊፍት፣ የሎ ካቢ፣ የዶር ዳሽ፣ ኡበር ኢትስ፣ ወዘተ) የሆኑ።
የሀሺሽ ዕጽ (Cannabis) ሱቆች፣ አርሶ አደሮች እና ማከፋፈያዎች።
በሲያትል የማዘጋጃ ቤት ሕግ 6.270መሠረት ንግዱ እንደ "የአዋቂ መዝናኛ" የሚተዳደር ነው
ተጨማሪ ድጋፍ

የንግድ ፈቃድን እንዴት ማዘመን እና የቢዝነስ እና የሥራ (B&O) ግብሮችን እዚህ እንደሚከፍሉ የበለጠ ይረዱ።

ስለ ምርጫ መመዘኛዎች እና የአሸላለም ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ድህረገፅ ይጎብኙ። ስለ አነስተኛ ንግዶች ድጋፍ ተጨማሪ መረጃ በከንቲባው ኮቪድ-19 ድርጣቢያ ላይ ይገኛል።

መደበኛ ዝመናዎች በ OED blog ላይ ተለጥፈዋል።

የቢዝነስ ባለቤቶች በኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት ድርጣቢያ OED website ላይ ለተገለጹት ተጨማሪ ሀብቶችም (ድጋፍ) ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል።

በዚህ ፕሮግራም በኩል ለገንዘብ ዕርዳታ የተመረጡ ንግዶች በ Safe Start Washington መመሪያዎች መሠረት እንደገና ለመክፈት እና ለመሥራት ቃል መግባት አለባቸው። ይህንን ማመልከቻ ለማጠናቀቅ ብቁ የሆነው የአነስተኛ ንግዱ ባለቤት ብቻ ነው እና ማንኛውም የሐሰት መረጃን የሚያቀርብ አመልካች በራስ-ሰር (በቀጥታ) ውድቅ ይሆናል።

የግላዊነት ማስታወቂያ

በዚህ የዳሰሳ ጥናት ውስጥ የቀረበው መረጃ የሕዝብ መዝገብ መረጃ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል እና ለሕዝብ ይፋ ሊሆን ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ የሕዝብ መዝገቦች ሕግ፣ RCW ምዕራፍ 42.56ን ይመልከቱ። መረጃዎን እንዴት እንደምናስተዳድር በበለጠ ለማወቅ፣ የእኛን የግላዊነት መግለጫ ይመልከቱ።

Next

# Seattle OED Business Stabilization Grant

እባክዎን ያስተውሉ፡ ይህ ሰነድ ለ 6 ኛ ዙር የንግድ ማረጋጊያ ስጦታ ማመልከቻ መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን እንደተጠናቀቀ ማመልከቻ መቅረብ የለበትም። ምንም የወረቀት ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም

## የንግድ መረጃ

**የንግድ ስም***

እባክዎን የንግድዎን ስም በሲያትል ከተማ የንግድ ፈቃድዎ ላይ እንደሚታየው ያስገቡ።

**የንግድ DBA (መሥራት ንግድ እንደ )**

በተለምዶ በወል በጣም የታወቀ ስምዎን። ምንም እንኳን፣ አንዳንድ ንግዶች DBA (የንግድ ሥራ ስም) ላይኖራቸው ይችላል።

**የተዋሃደ የንግድ መለያ (UBI) ቁጥር***

የድርጅትዎ የንግድ መለያ ቁጥር (UBI) 9 አሃዝ ያለው በስተይት ክፍሎች መታውቅያ ሆኖ በዋሽንግተን የንግድ ስራ እንዲያካሂዱ የሚፈቅድ ነው።

**የሲያትል የንግድ ፈቃድ የታክስ ሰርቲፊኬት ቁጥር***

ለዚህ የገንዘብ እርዳታ ስጦታ ብቁ ለመሆን ትክክለኛ የሲያትል የንግድ ሥራ ፈቃድ ያስፈልጋል። የፈቃድ ቁጥሮች ከ4-6 አሃዞች ናቸው። የፈቃድ ቁጥርዎን ለማግኘት ወደ ሲያትል የፈቃድ እና የግብር አስተዳደር ድህረገፅ https://www.seattle.gov/license-and-tax-administration/find-a-licensed-business ይሂዱ።

**የእርስዎን የሲያትል ከተማ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማግኘት አልቻልንም**

ማሳሰቢያ የከተማዎ ደንበኛ ቁጥር ያልተገኘ ይመስላል ፣ እባክዎን ለበለጠ መረጃ ከሲያትል ፋይናንስ (tax@seattle.gov) ወይም ከፋይል አካባቢያዊ መለያዎ ጋር ያረጋግጡ

**የእርስዎ ንግዶች 6 ዲጂት NAICS ኮድ ምንድነው?**

ትክክለኛውን የሲያትል የንግድ ፈቃድዎን በ [የፈቃድ እና የግብር አስተዳደር ድር ጣቢያ።]

123

**እራስዎን ጨምሮ፣ ንግድዎ ጠቅላላ ስንት ሠራተኞች (የትርፍ ሰዓት እና የሙሉ ጊዜ) አለው?***

123

**ሁሉም የተቀጠሩ ሠራተኞች (የንግድ ባለቤቱን ጨምሮ) በሳምንት ስንት ሰዓታት ይሠራሉ?***

እባክዎን የድርጅትዎ ስም ልክ በስያትል ከተማ የንግድ ፈቃድዎ እንደተጻፈው ያስገቡ

123

Back Next

# Seattle OED Business Stabilization Grant

እባክዎን ያስተውሉ፡ ይህ ሰነድ ለ 6 ኛ ዙር የንግድ ማረጋጊያ ስጦታ ማመልከቻ መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን እንደተጠናቀቀ ማመልከቻ መቅረብ የለበትም። ምንም የወረቀት ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም

## የገንዘብ ድጋፍ

**ለምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ ነው ለማመልከት የሚፈልጉት? (ማሳሰቢያ፡ የንግድዎን ገቢ ኪሳራ ለመወሰን የኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት ለ2019 እና ለ2020 የንግድ እና ሥራዎን (B&O) የግብር ምዝገባን ይገመግማል። የገቢ ኪሳራዎን ለማስላት፣ ንግድዎ የተቀበለውን ማንኛውንም የ COVID-ማቃለያ የገንዘብ ድጋፍ እንመለከታለን። የተጠየቀው የዕርዳታ ስጦታ መጠን ከገቢው ኪሳራ መጠን መብለጥ አይኖርበትም።)***

**Note:** Grant award is determined by calculated revenue loss between your businesses 2019 and 2020 gross annual revenue as reported on your city Business & Occupation (B&O) taxes.

**Example:**
2019 Gross annual revenue: $50,000
2020 Gross annual revenue: $30,000
Revenue loss: $20,000
**Maximum grant amount you are eligible for: $20,000**

- ○ $5,000
- ○ $10,000
- ○ $20,000

**እኔ (የንግዱ ባለቤት) የንግዴን የሲያትል ከተማ ንግድ እና የሥራ (B&O) የግብር ፋይል መረጃን ቅጂዎች እንዲያገኙ፣ እንዲገመግሙና እንዲያፀድቁ ለኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት ፈቃድ እሰጣለሁኝ።***

- ○ አዎ
- ○ አይ

**በ2020 ወይም በ2021 ንግድዎ፣ የቱንም ያህል ቢሆን፣ ምን ያህል ጠቅላላ የመንግስታዊ ብድር ዕርዳታ የገንዘብ ድጋፍ ተቀበለ? (ምሳሌዎች፡ የደመወዝ ከለላ ፕሮግራም (PPP)፣ የኢኮኖሚ ጉዳት የአደጋ ብድር፣ የአነስተኛ ንግድ ማረጋጊያ ፈንድ፣ ዋሽንግተን እየሠራ፣ የምግብ ቤት ማነቃቂያ ፈንድ ወይም የስኮላርሺፕ ጀንኪስ።)***

- ○ $0 ዶላር (ምንም የገንዘብ ድጋፍ አላገኘሁም)
- ○ ከዚህ ያነሰ $1,000
- ○ $1,001-$10,000
- ○ $10,001-$20,001
- ○ $20,001-30,001
- ○ $30,001-$40,000
- ○ $40,001-$50,001
- ○ ከላይ $50,001

Back | Next

amharic

# Seattle OED Business Stabilization Grant

## የምስክር ወረቀቶች

እባክዎን ያስተውሉ፡ ይህ ሰነድ ለ 6 ኛ ዙር የንግድ ማረጋጊያ ስጦታ ማመልከቻ መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን እንደተጠናቀቀ ማመልከቻ መቅረብ የለበትም። ምንም የወረቀት ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም

**ስለዚህ የዕርዳታ ስጦታ እንዴት ሰሙ?***

-

- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) ድህረገጽ
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) ብሎግ
- ማህበራዊ ሚዲያ
- የአነስተኛ ንግድ ምክር ቤት
- የንግድ ሥራ ማሻሻያ ማህበር
- የንግድ ድርጅት
- የአፍ ቃል
- ሌላ

**በዋሽንግተን ስቴት ሕጎች መሠረት በሐሰት ቅጣት ሥር ቀደም ሲል የተጠቀሰው እውነት እና ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ ወይም አውጃለሁ። የተሰጠው መረጃ ሁሉ ከሚመለከታቸው/ ከሚያገባቸው የስቴት ወይም የፌዴራል መንግስት ወኪል ድርጅቶች ሁሉ ጋር ይረጋገጣል። ይህ የሲያትል ንግድ እና ሥራ (B&O) የግብር አቅራቦት መረጃን ለመገምገም እና ለማረጋገጥ ፈቃድ መስጠትን ያካትታል። ይህንን ማመልከቻ ለእርዳታ በመፈረም እና በማስረከብ፣ በኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት በንግድዎ የቀረበውን የግብር መረጃ እንዲያገኝ እና እንዲገመግመው ፈቃድ እየሰጡ ነው።***

- አዎ
- አይ

## የማመልከቻው መጨረሻ

ሁሉም የተመረጡ አመልካቾች በአይአርኤስ ሰነዶች ላይ እንደተፃፈ የ EIN ቁጥራቸውን ፣ ስሙን እና የንግድ አድራሻቸውን መያዝ አለባቸው። ይህ በቢዝነስ ፌደራል ኤስ ኤስ -4 ቅጽ ፣ በ 2019 የፌዴራል የግብር ሰነዶች ወይም በ IRS ንግድ እና ልዩ የግብር መስመር (800) 829-4933 በመደወል (እባክዎን ከ 30 እስከ 60 ደቂቃ የመጠባበቂያ ጊዜ ይጠብቁ)።

Back Next

# Seattle OED Business Stabilization Grant

## የማመልከቻ መጨረሻ

እባክዎን ያስተውሉ፡ ይህ ሰነድ ለ 6 ኛ ዙር የንግድ ማረጋጊያ ስጦታ ማመልከቻ መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን እንደተጠናቀቀ ማመልከቻ መቅረብ የለበትም። ምንም የወረቀት ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም

### የማመልከቻ መጨረሻ

ሁሉም አመልካቾች ከኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት (OED) ኢሜል እስከ ጃንዋሪ 31፣ ቀን 2022 ይደርሳቸዋል። እርስዎ ከተመረጡ፣ ከኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት (OED) በ @seattle.gov አድራሻ ኢሜል ይልክልዎታል እና በስልክ ቁጥር እና በማመልከቻዎ ላይ በተጠቀሰው የኢሜል አድራሻ ከጧቱ 9 እስከ ምሽቱ 5ሰዓት (pm) ባለው ጊዜ ያነጋግርዎታል።

የከተማዎን የሲያትል የንግድ ሥራ ፈቃድ ማክበርን በተመለከተ ጥያቄዎች አሉዎት? ወደ TAX@seattle.govኢሜል ያድርጉ ወይም ወደ (206) 684-8484 ይደውሉ።

ከእርዳታ ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች እና ለተጨማሪ አነስተኛ የንግድ ሀብቶች (ድጋፍ) እባክዎን ይጎብኙ-

ጥያቄዎች? ወደ OED@seattle.gov ኢሜል ያድርጉ ወይም ወደ (206) 684-8090 ይደውሉ። ለተጨማሪ ሀብቶች (ድጋፍ) እባክዎን ይጎብኙ-

- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (OED) አነስተኛ ንግድ የመመሪያ መጽሐፍ
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት (OED) የኪራይ ውል ማሻሻያ መሣሪያ ስብስብ
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት (OED) የንግድ ሊዝ ማረጋገጫ ዝርዝር
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት (OED) አረንጓዴ የንግድ ፕሮግራም እና ኢንቫይሮስታርስ (Envirostars)
- የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት (OED) የምሽት ህይወት (የምሽት ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ወይም መዝናኛ) ማቋቋሚያ መመሪያ መጽሐፍ
- የምግብ ንግድ ፕሮግራሞች

Back Submit